# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መ/ቁ/251534
ሀምሌ 24 ቀን 2016 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ዋዚሞ ዋሲራ

ሠናይት አድነው

**አመልካች፡-** ኢትዮ አግሪ ሴፍት ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

**ተጠሪ፡-** አቶ በላይነህ ካሳሁን

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነበር መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሀምሌ 26 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመ/ቁ 127285 ሀምሌ 20 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአዊ ብሄረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የምእራብ አማራ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የሰጠውን ውሳኔ በማጽናቱ የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የስራ መደብ ምደባን መሰረት በማድረግ የቀረበ አቤቱታ ላይ የቀረበን የዳኝነት ሥልጣን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በምእራብ አማራ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ሲሆን በስር ፍ/ቤት አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ግንቦት 23 ቀን 2014ዓ.ም ባቀረቡት የክስ አቤቱታ በአመልካች ድርጅት በተለያየ የስራ መደብ ተመድቤ እየሰራሁ እያለሁ ተከሳሽ ድርጅት የሰራተኛ ማህበሩ በሌለበት ተግባራዊ ባደረገው መዋቅራዊ ምደባ በአስተዳደር ክለርክ ሊመድበኝ ሲገባ ከደረጃዬ ዝቅ በማድረግ በሁለገብ የጉልበት ሰራተኛ በማድረግ ምደባ ሰጥቶኛል ስለሆነም ተገቢው ምደባ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸምዓለማአየገለግልም!

አመልካች ሰኔ 8 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ጉዳዩ የግል የስራ ክርክር በመሆኑ ለቦርዱ በኣዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሰረት ከተሰጠው ስልጣን ውጪ በመሆኑ ቦርዱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም፤ በተጨማሪም ተጠሪ እበልጣቸዋለሁ የሚሏቸውን ሰዎች ማንነት እና በምን እንደሚበልጧቸው ወይም የስራ መደቡ ለምን ለሳቸው ሊሰጥ እንደሚገባ ገልጸው ያላቀረቡ ስለሆነ ክሱ ተሻሽሎ ሊቀርብ ይገባል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ቦርድም በአመልካች የቀረቡትን መቃወሚያዎች በብይን ውድቅ በማድረግ በፍሬ ነገር ግራቀኙን አከራክሮ እና ማስረጃ ሰምቶ ድርጅቱ በአዲስ የተሰራውን መዋቅር ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ መሰረት ተጠሪን ቀድሞ ይሰሩበት በነበረበት ቦታ ሊመድብ ሲገባ ያለመመደቡ ተገቢ አይደለም በማለት አመልካች ተጠሪን በአስተዳደር ክለርክ የስራ መደብ ከ18/4/2015ዓ.ም ጀምሮ መድቦ እንዲያሰራ እና ወጪና ኪሰራ በቁርጥ ብር 4,000.00 (አራት ሺ ብር) እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝቶ ይግባኙን በየደረጃው ለሚገኙ የበላይ ፍርድ ቤቶች ለአዊ ብሄረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ግራቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኃላ የምእራብ አማራ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የሰጠውን ብይን እንዲሁም ውሳኔ ሲያጸናው ሰበር ችሎቱ የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ሀምሌ 26 ቀን 2015 ዓ.ም በተጻፈ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም ተጠሪ ያቀረቡት ክርክር የግል የስራ ክርክር ስለሆነ ቦርዱ ጉዳዩን ተቀብሎ ለመወሰን የሥረ ነገር ስልጣን የለውም በማለት እና ክሱ ግልጽ ስላልሆነ ተሻሽሎ ሊቀርብ ይገባል በማለት ያቀረብነውን መከራከሪያ ውድቅ በማድረግ ተጠሪ በቀድሞ ስራ መደባቸው በአስተዳደር ክለርክ ተመድበው ሊሰሩ ይገባል በማለት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ በአጣሪው ችሎት ተመርምሮ የምእራብ አማራ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ጉዳይ የማየት ስልጣን ያለው መሆን አለመሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 1156/2011 እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 245837 ላይ ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንጻር ለማጣራት የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪ መጥሪያ የደረሳቸው ለመሆኑ ተረጋግጦ መልስ ያልሰጡ በመሆናቸው ችሎቱ ታህሳስ 24 ቀን 2016ዓ.ም በዋለው ችሎት የተጠሪን መልስ የመስጠት መብት በማለፍ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፣ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለው ግራ ቀኝ የሚከራከሩበትን ዋናዉን ጉዳይ ከማየቱ በፊት በሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ቦርዱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያለዉ መሆን አለመሆኑ በቀዳሚነት መታየት ያለበት መሆኑን የሚመለከት በመሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ .

የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 የስራ ክርክር እንደየጉዳዩ ዓይነት እና ባህርይ ለአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ ወይም ለሥራ ክርክር ችሎት ሊቀርብ የሚችልበትን ሁኔታ የሚደነግግ ሲሆን፣ የትኛዉ ዓይነት ጉዳይ ለየትኛዉ የዳኝነት አካል እንደሚቀርብ ለይቶ አስቀምጧል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 139 በፍርድ ቤት ሊታዩ ስለሚችሉ የስራ ክርክሮችን የሚደነግግ ሲሆን፣ የአዋጁ አንቀጽ 143 (1) (ለ) እስከ( ሽ) እንዲሁም አንቀጽ 147 የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን ይደነግጋሉ፡፡ በተለይም የአዋጁ አንቀጽ 145(1) ድንጋጌ የወል ስራ ክርክር ጉዳዮችን አከራክሮ የመወሰን ስልጣን በፌደራል እና ለክልል ለተቋቋሙ የአሰሪ እና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የተሰጠ መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት መረዳት የሚቻል ጉዳይ ነው፡፡በተያዘዉ ጉዳይ የተጠሪ ክርክር ያለአግባብ ከስራ መደቤ ዝቅ ተደረግኩኝ በማለት የተሰጣቸውን የስራ መደብ የሚመለከት ሲሆን፣ ከምደባ ጋር የተያያዙ ክርክሮች ለፍርድ ቤት እና ለቦርድ ሊቀርቡ የሚችሉበት ሁኔታ እንዳለ በአንቀጽ 139(1/ሠ)፣ በ 143(1/ሰ) እና 147 (1/ለ) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ ምደባን መነሻ ያደረገ ዳኝነት ለቦርድ ሊቀርብ የሚችለዉ ክርክሩ የወል ባህርይ ሲኖረዉ ብቻ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ በ143(1/ሰ) እና 148 (1/ለ) ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን፣ ለፍርድ ቤት የሚቀርበዉ ግን ክርክሩ የግል ባህርይ ሲኖረዉ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 139 (1) ያስረዳል፡፡ ስለሆነም ጉዳዩን ተቀብሎ ለማየት ቦርዱ ስልጣን ያለዉ መሆን አለመሆኑን በመወሰን ረገድ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የወል ባህርይ ያለዉ መሆን አለመሆኑን መወሰን ያስፈልጋል፡፡

በእርግጥ አዋጁ የወል የስራ ክርክርን አስመልክቶ የሰጠዉ ትርጉም የለም፡፡ ይሁንና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 18180 አንድን ክርክር የወል ወይም የግል

ብሎ በመወሰን ረገድ ግምት ዉስጥ ሊገቡ የሚገባቸዉን መስፈርቶችን አስመልክቶ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በዚህ ትርጉም መሰረት ክርክሩ የወል ለመባል የጋራ የሆነን የሠራተኞች መብትና ጥቅም የሚመለከት ሊሆን እንደሚገባ እና የወል የሚሰኘዉም ጉዳዩ የጋራ በሆነ የሠራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ዉጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነዉ፡፡ በአንፃሩ ክርክሩ የግል ነዉ የሚባለዉ ዉጤቱ በሠራተኛዉ መብት ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሲሆን ነዉ፡፡

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት ተጠሪ ለቦርዱ ባቀረቡት ክስ ለጠየቁት ዳኝነት መሠረት ያደረጉት በአመልካች ተፈጽሟል ያሉትን የስራ እና ደረጃ ምደባ የሚመለከት ነዉ፡፡ ይህ ደግሞ ተጠሪን በግል ያላቸውን መብት እና ተደረገ የተባለውን የምደባ ምክንያቶች በመመርመር ታይቶ ዉሳኔ የሚሰጥ ሲሆን፣ ዉጤቱም ከተጠሪ ዉጪ በሌሎች የአመልካች ሠራተኞች የጋራ ጥቅም ወይም መብት ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ዉጤት የሚያስከትል አይደለም፡፡ በመሆኑም የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ መሠረቱ የግል የስራ ክርክር እንጂ የወል የስራ ክርክር ነዉ ሊባል የሚችል አለመሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን ተቀብሎ ለማየት ስልጣን ያለዉ በአዋጁ አንቀጽ 139(1/ሠ) መሠረት የስራ ክርክር ችሎት እንጂ የአሠሪና ሠራተኛ ቦርድ አይደለም፡፡ በተጨማሪም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 245837 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ስለሆነም የምእራብ አማራ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ከዚህ አንፃር አይቶ አመልካች ያቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ዳኝነት ጥያቄ መመለስ ሲገባዉ በማለፍ የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሁም የአዊ ብሄረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንኑ ጠቅሶ የቦርዱን ዉሳኔ መሻር ሲገባዉ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የቀረበዉን የሰበር አቤቱታ በመሰረዝ የሰጠዉ ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ሌሎች በአመልካች እና ተጠሪ የቀረቡትን ክርክሮች መመርመር ሳያስፈልግ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመ/ቁ 127285 ሀምሌ 20 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአዊ ብሄረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የምእራብ አማራ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የሰጠውን ውሳኔ በማጽናቱ የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ትእዛዝ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1//ሀ/መሰረት መሰረት ተሽሯል ፡፡

2. የምእራብ አማራ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ይህን ጉዳይ ተቀብሎ ለማየት ስልጣን የለዉም ተብሎ ተወስኗል ፡፡
3. ተጠሪ ጉዳያቸውን ስልጣን ላለዉ ፍርድ ቤት የሚያቀርቡትን የዳኝነት ጥያቄ ይህ ዉሳኔ አይከለክልም፡፡
4. አመልካች በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**<u>ትእዛዝ</u>**

በዚህ መዝገብ ነሀሴ 5 ቀን 2015 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ተመላሽ ይደረግ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፅ/ወ

<u>ማስታወሻ</u>፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓለማአየገለግልም!